



# የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ መንግስት
# የጤናው ሴክተር የ2004 በጀት ዓመት
# የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ
# የአፈጻጸም ሪፖርት

*ሰኔ 2004 ዓ/ም*

ማውጫ

መግቢያ ........ 3
የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታ ስራዎቻችን ........ 5
የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ........ 6
የእናቶችና ህፃናት ጤና አገልግሎትን በሚመለከት ........ 8
ህብረተሰብ ዓቀፍ የተቀናጀ የህፃናት ህክምና አገልግሎት ........ 11
ስነ ምግብ ፕሮግራምን በተመለከተ ........ 12
የወባ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ተግባራት ........ 12
በትራኮማ ሳቢያ የሚከሰተውን ዓይነስዉርነት የመከላከልና የመቆጣጠር ስራ ........ 13
የኦንኮሴርኪያሲስ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር ........ 14
ሕብረተሰብ አቀፍ ቲቢ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር ........ 14
የአካባቢ ጤና አገልግሎት በሚመለከት ........ 14
የጤናና ጤና ነክ ድንገተኛ አደጋዎች ቅኝት ምላሽ ስራዎች ........ 15
ኤች አይ ቪ ኤድስ የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባራትን በሚመለከት ........ 15
የቲቢ በሽታን የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባራት ........ 18
የጤናው ሴክተር የፋይናንስ ሪፎርም ተግባራት ........ 19
የመድሃኒት እና የህክምና መሳሪያዎች አቅርቦት ........ 19
የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ማስፋፋት ........ 20
የጤናና ጤና ነክ አገልግሎቶችና ግብዓቶች ጥራት ቁጥጥር ተግባራት ........ 21
የህብረተሰብ የላቦራቶሪ ምርመራ ተግባራት ........ 24
የካፒታል በጀት አጠቃቀም ........ 25
የሰው ሃብት ልማት ........ 25
የጤና አመራር መረጃ ስርዓት ........ 26
የጥናትና ምርምርን ተግባራት ........ 26
ያጋጠሙ ችግሮች ........ 29

## መግቢያ

የ2004 ዓ/ም የጤናው ሴክተር እቅድ በክልል አቀፍ ለተነደፈዉ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድና ለምዕተ ዘመኑን የልማት ግቦች እንዲሁም አራተኛውን ዙር የጤናው ዘርፍ የልማት ፕሮግራሞች ለማሳካት በሚያስችሉ ፕሮግራሞች ላይ ትኩረት በመስጠት በየደረጃዉ ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ በክልሉ የሚገኙ ሁሉም ዞኖችና ወረዳዎች በቀጥታ ተሳትፈዉ የተዘጋጀ ሲሆን አፈጻጸሙንም ለማሻሻል እየተገነባ የሚገኘዉን የጤና ልማት ሰራዊት በመጠ ቀም ተንቀሳቅሰናል፡፡ በበጀት አመቱ የለውጥ ስራዎች የተቋማዊ በሆነ መልኩ እስከታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ ለማሳለፕ እንዲሁም ምርጥና የተሳኩ የጤናዉ ሴክተር ልምዶችን ወደ ሁሉም አካባቢዎች በማስፋፋት ላይ ያተኮሩ ስራዎችን ተሰርተዋል፡፡

የበጀት ዓመቱን ዕቅድ ለማሳካትና ህብረተሰቡን የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል በሴክተሩ የጤና ልማት ሰራዊት መገንባት ወሳኝ በመሆኑ የጤና ልማት ሥራችንን ህዝቡን በተለይም የሴቶችን አደረጃጀቶች በማብቃትና በተደራጀ ሁኔታ በማነቃነቅ የአመለካከት÷ የክህሎትና የግብአት አቅርቦት ማነቆዎችን በየደራጃዉ በመፍታት የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆቹን በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ ገቢራዊ ለማድረግ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በመሆኑም ከበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ጀምሮ የጤና ልማት ሰራዊት ቁመና በዝግጅትና በተግባር ምእራፍ ላይ የነበሩበትን ጉድለቶች በመገምገምና በተለዩ ዋና ዋና ማነቆዎች ላይ በየደረጃዉ ካለዉ አመራርና ፈፃሚዎች ጋር የጋራ ውይይት በማድረግና ቀጣይ አቅጣጫዎችን በማቀድ ሰፋፊ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ ስለሆነም የጤና ልማት ሰራዊት የበጀት ዓመቱ የጤና ልማት እቅድ ማስፈፀሚያ ቁልፍ መሳሪያ በማድረግ በዋና ዋና ፕሮግራሞች አፈጻጸም ላይ ተስፋ ሰጪ ውጤቶችን ለማስመዝገብ ተችሏል ፡፡

ይህም ሆኖ ያሳለፍነው በጀት ዓመት የጤና ልማት ሠራዊት ግንባታው ሲገመገም ከተወሰኑ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች በስተቀር የዝግጅት ምዕራፉን በጥራትና በተቀመጠዉ አቅጣጫ ያለመፈፀም፣ ሞዴል ቤተሰብ ስልጠና በጥራት ያለማከናወን፤ በአመራሩና በፈፃሚዎች ደረጃ የአመለካከት የድጋፍና የክትትል ማነቆዎች እንዲሁም ስራዎችን በዘመቻ መልክ የመፈፀም ዝንባሌዎች አሁንም የቀጠሉ ችግሮች ሲሆኑ ሰራዊቱን በተግባር ከመገንባት አንፃር ሲታይ በአንዳንድ ፕሮግራሞች በተለይም የእናቶች የወሊድ አገልግሎት ተጠቃሚነት ላይ የሚስተዋለዉን የአመለካከት ችግር ከመፍታት አንጻር መጠነኛ መሻሻሎች የታዩ ቢሆንም አሁን ጉድለት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ የለውጥ ሥራዎችን አፈጻጸም በሚመለከት ካለፉት ዓመታት በተሻለ ደረጃ ለመምራት ጥረት ተደርጓል፡፡ ለአብነት ያህል እያንዳንዱ የሥራ ሂደት በልማት ቡድንና በ1ለ5 አደረጃጀት በመቀናጀት ሥራዎችን ለመምራት ጥረት ተደርጓል፡፡ የክልሉ አመራሮች ዞኖችና ልዩ ወረዳዎችን ተከፋፍሎ በየሳምንቱ ሪፖርት በዋና ዋና ጉዳዮች በጋራ መድረክ እያቀረባቸው የሚገመገም ሲሆን በጋራ በተወሰኑና በተለዩ ጉዳዮች ላይ ግብረ መልስም እየተሰጠ ስራዎችን በተቀናጀ ሁኔታ ለመተግበር ጥረት ተደርጓል፡፡

የጤና ተቋማት በአቅራቢያቸው ከሚገኘው ህዝብ ጋር ቋሚ የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት ለአገልግሎት አሰጣጡ ጥራት መሻሻል አስተዋጽኦ ያላቸው በርካታ ተግባራት ከመከናወናቸውም በላይ የጤና ተቋማት ከህብረተሰቡ ጋር ያላቸው መቀራረብ ይበልጥ እንዲጠናከር ተደርጓል፡፡ ይህም ሆኖ የክልሉ አመራር ድጋፍ አልፎ አልፎ መቆራረጥ የሚያጋጥመው መሆኑ፤ የለውጥ ሥራዎችን በሙሉ ዕዉቀትና ክህሎት ከመምራት አንጻር አሁንም ጉድለት የሚታይበት መሆኑ፤ ከዞን አልፎ ወረዳዎችን ለይቶ ደካማ አፈጻጸም ያላቸውን ከማብቃት አንጻር ጉድለት የሚታይበት መሆኑ፤ በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ በታዩ ምርጥ ተሞክሮዎች መርካት በዚህ ረገድ የታዩ ችግሮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በሴክተሩ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትን ለመስበርና ሙስናን ለመዋጋት በርካታ ሥራዎች የተሰሩ ሲሆን ይህንንም ሥራ በስፋት አጠናክሮ ለመቀጠል እንዲረዳ የስነ ምግባር ሞኮንን በመሰየምና ለሥራ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በማሟላት በሙሉ አቅሙ ወደ ተግባር ለማስገባት ተችሏል፡፡ በሴክተሩ በሁሉም ደረጃዎች የሚገኘው ፈጻሚ መከተል የሚገባዉ የስነምግባር መመሪያ ተዘጋጅቶ በቢሮ ከሚገኙ ባለሙያዎች ጋር ሰፊ ጊዜ ተወስዶ ውይይት የተደረገበት ሲሆን በዞንና በልዩ ወረዳዎች እንዲሁም ለሁሉም ሆስፒታሎችና ለጤና ሳይንስ ኮሌጆች ሰነዱ ተልኮ ግብረ መልስ እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ የመንግስትን ሀብትና ንብረት አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ በቢሮ ደረጃ የዳሰሳ ጥናት ተካሂዶ መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮች ተለይተዉ የወጡ ከመሆኑም በላይ በየስራ ሂደቱ የሚገኙ ባለሙያዎች በጥናቱ ዉጤት ላይ ዉይይት አድርገው ችግሮቹ የሚስተካከሉበት ሁኔታ ላይ ከመግባባት በመድረስ ሥራዎች በዚሁ አግባብ እንዲመሩ ተደርጓል፡፡

የጸረ ኪራይ ሰብሳቢነት ትግሉንም ከማጠናከር አንጻር ሰራተኛው በየደረጃው ከኪራይ ሰብሳቢነት ጋር አያይዞ የአስተሳሰብ ትግል እንዲያደርግና የሚታዩ የኪራይ ሰብሳቢነት ችግሮችን በተደራጀ

ሁኔታ እንዲታገላቸው ለማድረግ በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ ከዚህ አልፈው በተለያዩ ደረጃዎች ጥፋት በፈጸሙት ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃዎች ከመወሰዳቸውም በላይ ሌሎችም ከዚሁ ትምህርት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

## የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታ ስራዎቻችን

የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታ ሥራችን ህዝባችንን በተደራጀ ሁኔታ በማነቃነቅና የአመለካከት የክህሎትና የግብአት አቅርቦት ማነቆዎችን በየደረጃዉ በመፍታት የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆቹን በተፋጠነ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግና ምርጥ ተሞክሮዎችን በማስፋት የህብረተሰቡን የጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት በላቀ ደረጃ ሊያረጋግጥ የሚችል ስልት በመሆኑ ከበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ጀምሮ በሴክተሩ እየተገነባ ያለዉን የጤና ልማት ሰራዊት በዝግጅትና በተግባር ምእራፍ የነበሩትን ጉድለቶች በመገምገምና በመለየት ሰራዊቱን ወደ ተግባራዊ ንቅናቄ በማስገባት በየደረጃዉ ላለዉ አመራርና ፈፃሚዎች የዕቅድ ኦሬንቴሽን በመስጠትና የጋራ መግባባት በመፍጠር ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

በዚህም መሰረት የደረጃው የተከናወኑ ተግባራትን አፈጻጸም የሁሉም ዞኖችና ልዩ ወረዳ ሃላፊዎች በተገኙበት በየሁለት ወሩ እየተገመገመ መሻሻል በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ቀጣይ አቅጣጫ እያስቀመጥን አፈጻጸሙን ስንከታተል የቆየን ከመሆኑም ባሻገር የጤና ልማት ሠራዊት ግንባታ ሂደት ያለበትን ደረጃ ለማወቅና ለመደገፍ የክልሉ የጤናዉ ሴክተር አመራሮችና ባለሙያዎች በቡድን እስከ ወረዳዎችና የአባወራ መኖሪያ ድረስ በመንቀሳቀስ ድጋፋዊ ክትትል በማድረግ በጎ ተሞክሮዎችን በመለየት፣ ድክመቶችና ዝቅተኛ አፈጻፀሞች እንዲሻሻሉ አስፈላጊው የሆኑ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል ፡፡

የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታ ህዝባችንን በተደራጀ ሁኔታ በማነቃነቅና የአመለካከት የክህሎትና የግብአት አቅርቦት ማነቆዎችን በየደረጃዉ በመፍታት የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆቹን በተፋጠነ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግና ምርጥ ተሞክሮዎችን በማስፋት የህብረተሰቡን የጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት በላቀ ደረጃ ሊያረጋግጥ የሚችል ስልት በመሆኑ በቀበሌ ደረጃ በተፈጠረው 1ለ5 ትስስር አማካይነት በበጀት አመቱ 1,021,532 ሞዴል እማዎራ/አባዎራዎች የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅን ሰልጥነዉና ተግባራዊ አድርገው ተመርቀዋል፡፡ በመሆኑም እስካሁን በድምሩ በክልሉ 1,960,425 (55%) ቤተሰቦች የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅን ሙሉ በሙሉ በመተግበር ሞዴል ሆነዋል፡፡ እንዲሁም ሰልጥነው በተመረቁ 505,198 ሞዴል የ1ለ5

ትስስር መሪዎች አማካኝነት 784,791 ቤተሰቦች ሥልጠና በመውሰድ ላይ ይገኛሉ፡፡ ሰልጥነው ለምረቃ የበቁትም በቀጣይነት ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች አማካይነት ክትትል እየተደረገላቸው ይገኛሉ፡፡

ይሁን እንጂ ከተወሰኑ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች በስተቀር የዝግጅት ምዕራፉን በጥራትና በተቀመጠዉ አቅጣጫ ያለመፈፀም፣ ሞዴል ቤተሰብ ስልጠና በጥራት ያለማከናወን፤ በአመራሩና በፈፃሚዎች ደረጃ የአመለካከት የድጋፍና የክትትል ማነቆዎች እንዲሁም ስራዎችን በዘመቻ መልክ የመፈፀም ዝንባሌዎች አሁንም ጎልተው የቀጠሉ ችግሮች ሲሆኑ ሰራዊቱን በተግባራዊ ተጠቃሚነት ከመገንባት አንፃርም ሲታይ በአንዳንድ ፕሮግራሞች በተለይም የእናቶች የወሊድ አገልግሎት ተጠቀሚነት ላይ የሚስተዋለዉን የአመለካከት ችግር ከመፍታት ላይ አሁንም ጉድለት ያለበት ሆኖ ታይቷል፡፡ እነዚህን ማነቆዎች በቀጣይ በፍጥነት ለማስተካከል በክልሉ አመራር በኩል ደካማ አፈጻፀም ያላቸዉን ዞኖችንና ወረዳዎችን ለይቶ የመደገፍ ስራ ተጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን ይህንኑ ከማጠናከር አንፃር በሁሉም እርከኖች የኮማንድ ፖስት በማደራጀት የተጀመረው ድጋፍና ክትትል ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

በበጀት ዓመቱ በማህበረሰብ ደረጃ የጤና ልማት ሠራዊት ግንባታን በአንጻራዊነት የተሻለ ሥራ የፈጸሙ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችንና ሞዴል ሆነው የተመረቁ ቤተሰቦችን በክልሉ ከሚገኙ 40 ወረዳዎች በመምረጥ ዕውቅና ተሰጥቷቸዋል፡፡ በዚሁ መድረክ ላይ የተመረጡ ምርጥ ተሞክሮዎች ከሁሉም ወረዳዎች ለተውጣጡ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ በመድረኩ ከየከተማው የመጡ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችም ተገኝተው ልምድ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ ከዚህ መድረክ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች አንዳቸው ከሌላዋ ልምድ የተለዋወጡበት፤ የተሻለ የሠሩ ዕውቅና ያገኙበትና ጤናማ የሥራ መንፈስና ውድድር በመካከላቸው እንዲፈጠር አስችሏል፡፡

## የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም

በበጀት ዓመቱ ተጨማሪ 28 ጤና ኬላዎች ግንባታቸዉ የተጠናቀቁና አገልግሎት መስጠት በመጀመራቸው በክልሉ በአሁኑ ጊዜ 3,631 ጤና ኬላዎች ይገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች በሴክተሩ እየተገነባ ላለዉ የጤና ልማት ሰራዊት የማይቆራረጥና ቀጣይነት ያለውን ድጋፍ እንዲሰጡ የሚጠበቅ በመሆኑ በተመደቡበት ቀበሌ ዉለዉና አድረዉ እንዲሰሩ ለማስቻል የጤና ልማት ሰራዊቱን በማነቃነቅ የመኖሪያ ቤት በሁሉም ቀበሌዎች

ለማስገንባት በታቀደዉ መሰረት በበጀት አመቱ ነባሮቹን የመኖሪያ ቤቶችን በማደስና አዳዲስ በመገንባት በድምሩ 1,841 የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የመኖሪያ ቤቶች ለአገልግሎት ዝግጁ ሲሆኑ በዚህም በክልሉ ማደሪያ ቤት ያላቸው የጤና ኬላዎች ሽፋን 51% ደርሷል። ይኸው የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የመኖሪያ ቤት አስፈላጊነት ለምንገነባው የጤና ልማት ሰራዊት ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ በህዝብ ንቅናቄ የመሩ አከባቢዎች እንደስልጤ፤ ደ/ኦሞና፤ ከፋ ዞኖች በአርአያት የሚጠቀሱ ሲሆኑ በሌሎች አከባቢዎች ይህ ተግባር በትኩረት ያልተመራ ስለሆነ ጉልህ ለዉጥ አልታየም።

የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የማሟያ ስልጠናን በተመለከተ በአንድ ቀበሌ ሁለት ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን የማሰማራት ተግባር ሙሉ በሙሉ የተፈፀመ ቢሆንም በተለያዩ ምክኒያቶች የተጓደሉትን ለሟሟላትና በአርብቶ አደሩ አከባቢዎች የጤና ኤክስቴንሽኑን ፕሮግራም ለማጠናከር አርብቶ አደሩን የመሰረታዊ ጤና አገልግሎቶች ተጠቃሚ ለማድረግ በሚደረገዉ ጥረት ባለፈው በጀት ዓመት አጋማሽ ጀምሮ 603 ሠልጣኞች የአንድ አመት ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ወደ ስራ ተሰማርተዋል። ከነዚህ ሰልጣኞች ዉስጥ 90ዎቹ ከደቡብ ኦሞ ዞን አርብቶአደር ወረዳዎች የተመለመሉ ናቸዉ። በተያያዘም በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶች የተጓደሉትን ለማሟላት 661 ዕጩ ሰልጣኞች ተመልምለው በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት ትምህርታቸዉን እየተከታተሉ ሲገኙ ከነዚህም ዉስጥ 180 ዎቹ በደቡብ ኦሞና ቤንች ማጂ ዞኖች ውስጥ ከሚገኙ አርብቶ አደር ወረዳዎች የተመለመሉ ናቸዉ።

የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈጻጸም ከማጠናከር አኳያ የሚመለከታቸውን አካላትና የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን በማሳተፍ ክልል አቀፍ የምክክር ጉባኤ ተካሂዷል። በምክክር ጉባኤው በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አተገባበርና አፈፃፀም ዙሪያ የታዩ ጠንካራ ጎኖች እና ክፍተቶች የተለዩ ሲሆን የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን በማስፋትና ድክመቶችን በማረም በየደረጃ ያለው አመራር አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት የጋራ መግባባት በተደረሰው መሠረት በክልሉ ባሉት ሁሉም ከተሞች ፕሮግራሙን በጤና ልማት ሠራዊት ግንባታ ማእቀፍ በመኖሪያ ቤት አካባቢ፤ በትምህርት ቤቶች፤በወጣት ማእከላትና በማረሚያ ቤቶች ህብረተሰቡ ፓኬጆቹን በተደራጀ ሁኔታ ተጠቃሚ እንዲሆን ጥረት ተደርጓል። በዚህም በበጀት ዓመቱ በከተሞች ፓኬጁን ተግባራዊ አድርገው በድምሩ 40,839 ሞዴል ቤተሰቦች ተመርቀዋል።

የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ተደራሽነት 100% ለማድረስ በበጀት ዓመቱ 242 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባሙያዎችን ስልጠና ለመስጠት የታቀደ ቢሆንም የብቃት ፈተና ያለፉት 54 ጤና ባለሙያዎች ስልጠና በመውሰድ ላይ ይገኛሉ ፡፡

የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የተሀድሶ ስልጠና ለሠራተኞቹ የክህሎት ማነቆዎችን በመፍታት ጥራት ያለዉ አገልግሎት ለህብረተሰቡ እንዲሰጡ የሚያስችላቸዉ ሲሆን ይኼው ስልጠና በተቀናጀ ሁኔታ የሚሰጥ በመሆኑ ተደጋጋሚ የስልጠና ጥሪዎች በማስቀረት እየገነባን ላለው የጤና ልማት ሰራዊት ተከታታይ ድጋፍ በመስጠት ሰራዊቱን በተግባራዊ ንቅናቄ ለመገንባት ትልቅ ፋይዳ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሁሉንም የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በተሃድሶ ስልጠና ለማሰልጠን በታቀደው መሰረት በሁሉም የገጠር ቀበሌዎች የሚገኙ 7,390 የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ስልጠናውን ተከታትለዋል፡፡

በበጀት አመቱ ለ944 ጤና ኬላዎች የህክምና ቁሳቁስ የገባላቸው ሲሆን ይህም በክልሉ የህክምና ቁሳቁስ የገባላቸውን ጤና ኬላዎችን ብዛት 2,996 ያደርሰዋል በመሆኑም በክልሉ የተሟላ የህክምና ቁሳቁስ የገባላቸው ጤና ኬላዎች ሽፋን 83% ደርሷል፡፡ በተጨማርም በበጀት አመቱ በጤና ኬላ ደረጃ ለሚሰጡት አገልግሎቶች የወባ፤ የሳምባ ምች፤ የምግብ እጥረት፤ የቤተሰብ ምጣኔ እና ሌሎችም ግብአቶች ሳይቆራረጥ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

## የእናቶችና ህፃናት ጤና አገልግሎትን በሚመለከት

የእናቶችና ህጻናትን ጤና አገልግሎቶችን አጠናክሮ መተግበር በሀገራችን የተጀመረውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንዲሁም የምዕተ ዓመቱን የልማት ግብ ለማሳካት የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በክልላችን የእናቶችና ሕፃናት ጤንነት ወይም ደህንነት ሁኔታ ማሻሻል እንዲቻል ለጤና ልማት ሰራዊት ግንባታ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በየደረጃው የተጠናከረ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል፡፡

የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትን ማስፋፋትና ማጠናከር ሀገራችን ካላት የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ጋር የተመጣጠነ ህዝብ ዕድገት እንዲኖር ከማስቻሉም በላይ ለዜጎች የሥነ ተዋልዶ ጤና ደህንነት ሁኔታ መሻሻል ከፍተኛ ሚና እንዳለው ይታመናል፡፡ ስለሆነም የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚነት መጨመር በዋናነት የእናቶችንና ሕፃናትን የህመምና የሞት መጠን መቀነስ ይቻላል፡፡ ስለዚህም የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶችን ከሚያስፈልጉ አማራጭ የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ ግብዓቶች ጋር ተጠቃሚዎች በሚመርጡትና በወሰኑት ዓይነት፣ በፈለጉት

ቦታና ጊዜ ተደራሽ በማድረግ የተጠቃሚዎችን ቁጥር መጨመር ወሳኝ ጉዳይ አድርጎ በመውሰድ እየተሠራ ይገኛል፡፡ በበጀት ዓመቱም በክልሉ አገልግሎቱን ለመስጠት ከታቀደው 2,527,091 ሴቶች ውስጥ 2,171,468 ሴቶችን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለማድረግ የተቻለ ሲሆን በበጀት አመቱ አገልግሎቱን ማግኘት ከሚገባቸው አጠቃላይ እናቶች አንጻር ሽፋኑ 64% ደርሷል፡፡ የረዥም ጊዜ አገልግሎትን ለህብረተሰቡ በስፋት ለማዳረስ ከተያዘው ዕቅድ መነሻ ኢምፕላኖን የተባለውን የረዥም ጊዜ የእርግዝና መከላከያ ዘዴ በክንድ ስር የማስገባት ሥልጠና ካለፈው ዓመት ጀምሮ እየተሰጠ ይገኛል፡፡ በዚህም በክልሉ በአጠቃላይ 92,630 ሴቶችን የረጅም ለረጊዜ የሚቆይ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ ተጠቃሚ ለማድረግ ተችሏል፡፡

ከእርግዝናና ከወሊድ ጋር በተያያዘ የሚታመሙና የሚሞቱ እናቶችን ቁጥር ለመቀነስ የቅድመ ወሊድ፣ የወሊድና ድህረ ወሊድ ጤና አገልግሎቶችን ተደራሽና ተጠቃሚ ማድረግ አስፈላጊና ወሳኝ በመሆኑ የጤናው ሴክተር ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በስፋት እየተሠራበት ይገኛል፡፡ ከእነዚህም መካከል የህብረተሰቡን ግንዛቤ የማሳደግ፣ የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን የማስፋፋት የማጠናከርና የግብዓት አቅብሮትን የማረጋገጥ እንዲሁም የባለሙያዎችን ክህሎት የማሻሻል ተግባራት ዋነኞቹ ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት እናቶች ወደ ጤና ተቋማት መጥተው እንዲወልዱ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ጤና ጣቢያና ሆስፒታል መምጣት ላልቻሉት በአቅራቢያቸው በሚገኙ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች አማካይነት አገልግሎቱን በጤና ኬላ ደረጃ እንዲያገኙ እየተደረገ ይገኛል፡፡

በዚህም በበጀት አመቱ የቅድመ ወሊድ ክትትል አገልግሎትን ማግኘት ከሚጠበቅባቸው 669,039 መካከል 600,371 እናቶች አገልግሎቱን ያገኙ ሲሆን ይህም በበጀት አመቱ አገልግሎቱን ማግኘት ከሚገባቸው እናቶች 90% ይሆናል፡፡ በበጀት አመቱ በጤና ተቋማት የወሊድ አገልግሎትን ለ434,875 እናቶች ለመስጠት ታቅዶ በክልሉ በሚገኙ በመንግስት የጤና ተቋማት ውስጥ 258,134 እናቶች አገልግሎቱን ያገኙ ሲሆኑ ይህም በበጀት ዓመቱ አገልግሎቱን ለማዳረስ ከታቀደው አንጻር 59% መሠራቱን ያሳያል፡፡ ከእነዚህም መካከል 140,169 ያህል እናቶች አገልግሎቱን ያገኙት በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች አማካይነት ነው፡፡ በሌሎችም ባለሙያዎች ድጋፍ በጤና ተቋማት የወለዱ እናቶች ቁጥር 117,906 ሲሆን ይህም ካለፉት ዓመታት መጠነኛ መሻሻል አሳይቷል፡፡

በሌላ ረገድ በክልላችን የቅድመ ወሊድ ክትትል የሚጀምሩ እናቶች ቁጥር በርካታ ቢሆንም አንድ እናት በአንድ የእርግዝና ወቅት ቢያንስ አራት ጊዜ በባለሙያ መታየት የሚገባት ከመሆኑ አንጻር ሲታይ ነፍሰጡር እናቶች በባለሙያ የመታየት ልምድ አነስተኛ መሆኑና በጤና

ተቋማት የመውለድ ዝንባሌዎች ገና በብዙ ያልዳበረ በመሆኑን ያሳያል፡፡ በጤና ተቋማት ላይ የሚሰጠው የወሊድ አገልግሎት አንጻር አነስተኛ አፈጻም ያስመዘገቡ አካባቢዎች እንደ ከፋ፣ ጌዲኦ፣ ሲዳማና ደቡብ ኦሞ ዞኖች እና ባስኬቶና የም ልዩ ወረዳዎች ሲሆኑ ሀዋሳ ከተማ አስተዳደር፣ ከንባታ ጠንባሮ፣ ጉራጌ ጋሞጎፋ፤ ወላይታ ዞኖች እና ኮንታ ልዩ ወረዳ በመጠኑም ቢሆን የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ናቸዉ፡፡

በበጀት ዓመቱ የቲቢ በሽታ መከላከያ /ቢሲጂ/ ክትባት አገልግሎትን እድሜያቸዉ ከ1 አመት በታች ለሆኑ 635,587 ለመስጠት ታቅዶ ለ597,843 ህጻናት ለመስጠት የተቻለ ሲሆን ይህም ለበጀት አመቱ ከታቀደዉ እቅድ 94% ይደርሳል፡፡ በበጀት አመቱ የፔንታቫለንት ሦስት ክትባትን ለ576,314 ህጻናት ለመስጠት ታቅዶ ለ545,749 ህጻናት ለመስጠት የተቻለ ሲሆን ይህም በበጀት አመቱ አገልግሎቱን ማግኘት ከሚጠበቅባቸዉ ህፃናት አንፃር ሽፋኑ 95% ይደርሳል፡፡ በተመሳሳይም የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባትን 576,314 ለመስጠት ታቅዶ ለ533,372 ህጻናት ለመስጠት የተቻለ ሲሆን ይህም ለበጀት አመቱ አገልግሎቱን ማግኘት ከሚጠበቅባቸዉ ህፃናት አንፃር ሽፋኑ 88% ይደርሳል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የህጻናት የህመምና ሞት ግንባር ቀደም ምክንያት ለሆነዉ ለሳምባ ምች መከላከያ ክትባት በክልላችን በጥቅምት ወር በይፋ የተጀመረ ሲሆን ክትባቱን በተሳካ ሁኔታ የመደበኛ ክትባት መርሀ ግብር አካል ለማድረግ ተችሏል፡፡ በበጀት አመቱ ፒ.ሲ.ቪ.3 ክትባት ለ179,791 ህጻናት የተሰጠ ሲሆን አገልግሎቱን ማግኘት ከሚገባቸው ህጻናት መካከልም ሽፋኑ 62% መሆኑን ያመለክታል፡፡

በክልሉ የመደበኛ ክትባት ሽፋን መስራት ከነበረበት አንጻር ሲታይ እንደ ከንባታ ጠንባሮ፣ ሲዳማ፣ ስልጤና እና ወላይታ ዞኖች የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ሲሆኑ ይሄዉ ተግባር በአግባቡ ያልተመራባቸዉና ሽፋኑ እጅግ ዝቅተኛ ከሆነባቸው አከባቢዎች መካከል የሰገን አካባቢ ህዝቦች፤ የጌዴኦና የሸካ ዞኖች እና የባስኬቶ ልዩ ወረዳ ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በበጀት አመቱ በእነዚሁ አከባቢዎች የተከሰተዉ የኩፍኝ ወረርሽኝ የአገልግሎት አሰጣጡ ተደራሽነት፣ የጥራት ጉድለት እና የክትትልና ድጋፍ ማነስ ዉጤት መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የክትባት መጠነ ማቋረጥ በተመለከተ አገልግሎቱን ጀምረዉ ያቋረጡት ህጻናት መጠን 8% ቢሆንም የክትባት አገልግሎት በአግባቡ ባልተመራባቸዉና ስራዎችን በሰራዊት ማዕቀፍ ባልተፈጸመባቸው አካባቢዎች ሕጻናትን ተከታትለዉ ክትባት ማስጨረስ ባለመቻላቸዉ እንደ ጌድኦና የሰገን አከባቢ ህዝቦች ዞኖች እንዲሁም በባስኬቶ ልዩ ወረዳ ባሉ የክትባት መጠነ

ማቋረጥ ከሚጠበቀዉ በላይ ሆኖ ታይቷል፡፡ ይህም ሁኔታ ከፍተኛ የሆነ የክትባት ብክነትና ለወረርሽኝ መከሰት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር በመሆኑ በቀጣይነት መስተካከል ያለበት ይሆናል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ዓመት የኩፍኝ በሽታ በወረርሽኝ መልክ በተከሰተባቸው 9 ዞኖች (ካፋ፣ ሸካ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ ሲዳማ፣ ሐዲያ፣ ጋሞጎፋ፣ ደ/ኦሞ፣ ሰገን፣ ወላይታ) ዞኖች ውስጥ በሚገኙ 31 ወረዳዎች የኩፍኝ ክትባት እድሜያቸዉ ከ 6 ወር እስከ 5 አመት ለሆኑ 1,704,993 ህፃናት በዘመቻ ክትባቱን ለመስጠት ታቅዶ 1,646,942 ህፃናት ለመከተብ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 96% ነው፡፡ ዓለም አቀፍ የፖሊዮ በሽታን ሥርጭትን ለመግታት በተያዘው ዕቅድ መሠረት በደቡብ ኦሞና ቤንች ማጂ ዞኖች የፖሊዮ መከላከያ ክትባት በሁለት ዙር ከአምስት አመት በታች ለሆኑ ህፃናት ተሰጥቷል፡፡

የክትባት አገልግሎትን ጥራት ለመጠበቅ የክትባት የቅዝቃዜ ሰንሰለት መጠበቂያ መሣሪያዎችን ደህንነት አስተማማኝ ማድረግና እክል ሲገጥማቸውም በፍጥነት ጠግኖ አገልግሎት ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ በክልሉ በሁሉም አከባቢዎች የሚገኙ 166 የክትባት ቅዝቃዜ ሰንሰለት አጠባበቅ ባለሙያዎች የሪፍሪጅሬተር ጥገና ሥልጠና የተሰጣቸው ከመሆኑም በላይ ሲበላሹ ወዲያው መጠገን እንዲችሉ 20 የሪፍሪጅሬተር መጠገኛ መሣሪያዎች ኪት ተገዝቶ ለዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ተሰጥቷቸዋል፡፡

## ህብረተሰብ ዓቀፍ የተቀናጀ የህፃናት ህክምና አገልግሎት

ለህፃናት ሞት ህመምና ስቃይ ቀዳሚ ምክንያት የሆኑት ሳምባ ምች፤ ተቅማጥ፤ ወባ እና የምግብ እጥረት እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዳችን የህፃናትን ሞት ለመቀነስ የተቀመጠዉን ግብ ለማሳካት ከላይ የተጠቀሱትን የጤና ችግሮችን የሚያስወግዱ የጤና አገልግሎቶችን ተደራሽነትና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ወሳኝ ይሆናል፡፡ ባለፈዉ አመት የጀመርነዉ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ስልጠና በበጀት ዓመቱም የቀጠለ ሲሆን 390 የጤና ባለሙያዎችና 4050 የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ሥልጠናውን ወስደው ወደ ሥራ ተሰማርተዋል፡፡ በመሆኑም በአሁን ወቅት በክልሉ በሁሉም አካባቢዎች የሚገኙ ጤና ኬላዎች በግብአት ተሟልተዉ በጤና ጣቢያ ባለሙያዎች በድጋፋዊ ክትትል እየታገዙ የተቀናጀ የህፃናት ህክምና አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

## ስነ ምግብ ፕሮግራምን በተመለከተ

በሥነ ምግብ ዙሪያ በበጀት ዓመቱ በአንድ ዙር እድሜያቸው ከ6 ወር እስከ 59 ወራት ለሆናቸው ህፃናትና ለነፍሰ ጡር እናት በ37 ወረዳዎች የምግብ ዕጥረት ያለባቸውን የመለየት ስራ ተከናውኗል። በዚህም መሠረት ለ213,859 ነፍሰጡርና አጥቢ እናቶች ምልመላ ለማካሄድ ታቅዶ ለ205,333 /96%/ ልየታ የተሠራላቸው ሲሆን በዚህም ልየታ የምግብ እጥረት የታየባቸው 36,103 እናቶች ተገቢው የአልሚ ምግብ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። እድሜያቸው ከ6 ወር እስከ 59 ወራት ለሆናቸው 764,408 ህፃናትን የምግብ እጥረት ልየታ ለመሥራት ታቅዶ 791,845 ልየታ የተሠራላቸው ሲሆን የምግብ እጥረት ችግር ያለባቸው 16,671 ህፃናት በጤና ድርጅቶች ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል።

ከዚህም በተጨማሪ የህጻናትን ሞት ከመቀነስ እና በሽታን ከመከላከል አንጻር ያለው ሚና ከፍተኛ የሆነውን የVit A ንጥረ ነገር እድሜያቸው ከ6 እስከ 59 ወራት ለሆናቸው ለ2,474,477 ሕፃናት ለመስጠት ታቅዶ 2,440,788 አገልግሎቱን ያገኙ ሲሆን አፈፃፀሙም 99% ነው። ለሁለተኛ ዙር በየካቲት ወር በተደረገው ተመሳሳይ ዘመቻም 2,423,325 ህጻናት የቫይታሚን ኤ እንክብል ያገኙ ሲሆን አፈጻጸሙ 101.5% ሆኗል። እንዲሁም ፀረ-የሆድ ውስጥ ጥገኛ ትላትሎች መድኃኒት ዕድሜያቸው ከ24 ወር እስከ 59 ወር ለሆኑ 1,851,420 ሕፃናት ለመስጠት ታቅዶ 1,736,124 ህጻናት አገልግሎቱን ያገኙ ሲሆን አፈፃፀሙ 94% ይሆናል።

## የወባ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ተግባራት

የወባ በሽታ መከላከያና ቁጥጥር ተግባራትን በሚመለከት በበጀት ዓመቱ የተጠናከረና የተቀናጀ የመከላከልና የቁጥጥር ስራዎች የተሠሩ ቢሆንም ወቅቱን ካልጠበቀ ዝናብ ጋር በተያያዘ እና በበጋ ወራት በተሰሩ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች በርካታ የወባ ትንኝ መራቢያ ቦታዎች በመፈጠራቸውና እንደአልጋ አጎበር ያሉ የወባ መከላከያ ዘዴዎችን በአግባቡ ክትትል በማይደረግባቸዉ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች የወባ ህሙማን ቁጥር ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የመጨመር አዝማሚያ ያሳየ ቢሆንም በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመቆጣጠር ተችሏል። ለወባ ታማሚዎች ቁጥር መጨመር ምክንያት የነበሩት ወቅቱን ባልጠበቀ ዝናብ ምክንያት በተለያዩ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች የወባ ትንኝ መራቢያ ቦታዎች በመፈጠራቸው በተለይ በሲዳማ፣ በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር፣ በወላይታ፣ ደቡብ ኦሞ፣ በሀዲያ እና በከምባታ ጠምባሮ ዞኖች የወባ ህሙማን ቁጥር ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ስነጻጸር የመጨመር አዝማሚያ አሳይቷል።

የመከላከሉን ስራ ለማጠናከር በበጀት አመቱ 995,731 አጎበሮች ያረጁትን ለመተካት በክልላችን ዉስጥ በጣም ተጋለጭ ለሆኑ ወረዳዎች ቅድሚያ በመስጠት ስርጭት ተከናዉኗል፡፡ በስርጭቱም ወቅት በየቀበሌው በተደራጀዉ የልማት ቡድንና የ1ለ5 አደረጃጀት ስለአጠቃቀሙ ትምህርት የተሰጣቸዉ ቢሆንም ተካታታይነት ያለው ግንዛቤ የማስጨበጥና የክትትል ሥራ የሚፈልግ ተግባር ነው፡፡

በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ ዉስጥ 913,725 ሰዎችን በተለይ የተፈጠረውን የጤና ልማት ሠረዊት በማነቃነቅ በአካባቢ ቁጥጥር ስራ በማሳተፍ **520,416** ካ.ሜ ጊዜያዊና **153,003** ካ.ሜ ቋሚ የወባ ትንኝ መራቢያ ቦታዎችን የማፋሰስና የማዳፈን ስራ ተከናውኗል፡፡ በመራቢያ ቦታዎችም **31,877** ሲ.ሲ አቤት ኬሚካልና **16** ሊትር የተቃጠለ የሞቶር ዘይት በመርጨት የወባ ትንኝ ዕጭ ቁጥጥር ስራ ተሰርቷል፡፡

የወባ በሽታ የምርመራና የህክምና አገልግሎትን በሚመለከት በበጀት ዓመቱ **840,706** ሰዎች በላብራቶሪ ምርመራ ተካሂዶ የወባ በሽታ ተገኝቶባቸው ህክምና ያገኑ ሲሆኑ ተመርምረዉ ወባ ከተገኘባቸዉ ዉስጥ 508956 /61%/ ኘ/ፋልስፋረም እና 275478 /33%/ ኘ/ቫይቫክስ ናቸዉ፡፡

የአካባቢ ጤና አገልግሎት በሚመለከት የሳኒቴሽን ሽፋን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ሲሆን በ2004 በጀት አመት ቀደም ሲል ተሰርተው በተለያዩ ምክንያቶች ከአገልግሎት ውጭ የሆኑትን በአዲስ መልክ ለመተካት **105,056** መፀዳጃ ቤቶች በቤተሰብ ደረጃ ተሰርተው አገልግሎት እንዲሰጡ በመደረጉ በዚህም **514,774** ሰዎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተደረገ ቢሆንም መጸዳጃ ቤቶችን ማሟላት ሚገባቸዉን የጥራት ደረጃ ከማስጠበቅና መጸዳጃ ቤትን የመጠቀም ባህል እስካሁን በሚፈለገዉ መጠን ያልዳበረ ነው ፡፡

## በትራኮማ ሳቢያ የሚከሰተውን ዓይነስዉርነት የመከላከልና የመቆጣጠር ስራ

በትራኮማ ሳቢያ የሚከሰተውን ዓይነስዉርነት ለመከላከልና ለመቆጣጠር ከሚመለከታቸው አጋሮች ጋር በመሆን ቀደም ባሉት ዓመታት ከበሽታ ጫና አንጻር ተመርጠው ልዩ ድጋፍ ሲደረግላቸው የቆዩ በጉራጌ፣ በወላይታ፣ በጋሞጎፋ እና ከፊል ስልጤ ዞኖች በሚገኙ ወረዳዎች ላይ ድጋፉ የቀጠለ ሲሆን በጤና ተቋማት በቋሚና ዉሎ ገባ ጣቢያዎች ከሚደረግላቸው የዓይን ሕክምና በተጨማሪ በጤና ኤክስቴሽን ሠራተኞችና በልማት ቡድን መሪዎች አማካይነት ዚትሮመክስ (zithromax) የሚባል በዓመት አንድ ጊዜ የሚሰጥ መድሃኒት በበጀት አመቱ ከ2.4 ሚሊዮን በላይ የችግሩ ተጠቂ የሆኑ ከበሽታ እንዲጠበቁ ተደርጐል፡፡

## የኦንኮሴርኪያሲስ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር

በክልላችን ኦንኮሴርኪያሲስ የሕብረተሰቡ የጤና ችግር በሆነበቸው የምዕራብ ዞኖቻችን ማለትም ካፋ፣ ሸካ እና ቤንች ማጂ ዜጐች ላለፉት ዓመታት ሲሰጥ የቆየው ፀረ ኦንኮሴርኪያሲስ እጭ መድሃኒት /ሜኪታዝን/ በዓመት አንድ ጊዜ የሚካሄደው አደላ በዘንድሮ በጀት ዓመትም በተቀመጠው የጊዜ ሠሌዳ መሠረት እየተሰጠ ያለ ሲሆን ለአፈጻጸሙም ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል፡፡

## ሕብረተሰብ አቀፍ ቲቢ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር

ቲቢ በሽታን በመከላከልና በመቆጣጠር ሕብረተሰቡ ጤናማና አምራች እንዲሆን ለማስቻል ሥርጭቱን ለመግታት እንደዋነኛ መፍትሄ የተቀመጠው ሕብረተሰቡን ስለ በሽታው ግንዛቤና ክህሎት ማስጨበጥ ሲሆን በዚህ ረገድ በሙከረ ደረጃ በሲዳማ ዞን በሚገኙ በሁሉም ጤና ኬላዎች እየተተገበረ ያለው ከሦስት ሳምንት በላይ ሳል ያለው ታማሚ የቤተሰብ አባል አክታ ወደ ጤና ጣቢያ በመወሰድና በተገኘው ዉጤት መሠረት ፀረ ቲቢ መድሃኒት ጨርሶ እንዲወስድ የሚደረገው ክትትል ጥሩ የሚባል ዉጤት እያሳየ ስለሆነ በቀጣዩ በጀት ዓመትም ለሁሉም የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች በዋና ዋና ተላላፊ በሽታዎች የተቀናጀ የተሃድሶ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጎ ተሞክሮዉ በሁሉም ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች የሚተገበርበት ሁኔታ የሚመቻች ይሆናል፡፡

## የአካባቢ ጤና አገልግሎት በሚመለከት

የአካባቢ ጤና አገልግሎት በሚመለከት የሳኒቴሽን ሽፋን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ሲሆን በ2004 በጀት አመት ቀደም ሲል ተሰርተው በተለያዩ ምክንያቶች ከአገልግሎት ውጭ የሆኑትን በአዲስ መልክ ለመተካት **105,056** መፀዳጃ ቤቶች በቤተሰብ ደረጃ ተሰርተው አገልግሎት እንዲሰጡ በመደረጉ በዚህም **514,774** ሰዎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተደረገ ቢሆንም መጸዳጃ ቤቶችን ማሟላት ሚገባቸዉን የጥራት ደረጃ ከማስጠበቅና መጸዳጃ ቤትን የመጠቀም ባህል እስካሁን በሚፈለገዉ መጠን ያልተሻሻለ ተግባር ነዉ፡፡

የጤና ልማት ሰራዊቱን በማጠናከርና በመጸዳጃ ቤት ከአጠቃቀም አንፃር የሚታዩ ማነቆዎችን በመፍታት 1437 ዕጹ የገጠር ቀበሌያትን ለመፍጠር ታቅዶ የነበረ ሲሆን በበጀት አመቱ 728 ቀበሌያት ሜዳ ላይ ከመፀዳዳት ነጻ በመሆናቸው በክልሉ በአጠቃላይ ሜዳ ላይ ከመጸዳዳት ነፃ

የሆኑ ቀበሌያት ብዛት 985 ደርሰዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በወላይታ ዞን የሶዶ ዙሪያ ወረዳና በጉራጌ ዞን የጉመር ወረዳ ቀበሌዎቻቸዉን ሙሉ በሙሉ ጽዱና ከሜዳ ላይ መፀዳዳት ነፃ በማድረግ በወረዳ ደረጃ በማሳወጅ ግንባር ቀደም ስፍራን ይዘዋል፡፡

## የጤናና ጤና ነክ ድንገተኛ አደጋዎች ቅኝት ምላሽ ስራዎች

በክልላችን የማህበረሰብ አቀፍ የጤናና ጤና ነክ ድንገተኛ አደጋዎች ቅኝትና ምላሽ አተገባበር ቀደም ሲል በሁለት ወረዳዎች ሙከራ ትግበራ ተካሂዶ ወደ ሰባ ወረዳዎች በማስፋት ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ የበሽዎች ቅኝት የተዘረጋ በመሆኑ አበረታች ውጤት በማሳየት ላይ ይገኛል፡፡ በበጀት ዓመቱ በክልላችን በ4 ዞኖች የኩፍኝ ወረርሽኝ ተከስቶ የነበረ ሲሆን በወረርሽኙም ክስተት በከፋ ዞን 1716፣ በሰገን አካባቢ ሕዝቦች ዞን 540፣ በደቡብ አሞ ዞን 93 እና በጋሞ ጐፋ ዞን 3458 ህፃናት በድምሩ 5857 ህፃናት የተጠቁ ሲሆን ችግሩ እንዳይሰፋም አስፈላጊው ድጋፍና ክትትል በማድረግ ወቅታዊ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

በበጀት አመቱም የተቀናጀ የበሽታዎች ቅኝት ሪፖርት ወቅታዊነትና ምሉዕነት እንዲሻሻል በተደረገው ጥረት በወቅቱ ሪፖርት የሚያደርጉ ጤና ተቋማት ቁጥር የጨመረ ሲሆን ደቡብ አሞ፣ ጋሞ ጐፋ፣ ጌዲኦ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ የሰገን አካባቢ ሕዝቦች ዞኖችና ኮንታና የም ልዩ ወረዳዎች ከሳምንታዊ ሪፖርት ወቅታዊነትና ሙሉእነት ችግር ያልተሻገሩ ሲሆን እነዚህን ጉድለቶች ለመቅረፍ በቀሪ ወራት ትኩረት በመስጠት የምንፈፅማቸው ተግባራት ይሆናሉ፡፡

## ኤች አይ ቪ ኤድስ የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባራትን በሚመለከት

ኤች አይ ቪ ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባራትን በሚመለከት የማህበረሰቡን አቅም በማጎልበትና ግንዛቤውን በማሳደግ ቫይረሱ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ መቋቋም የሚችል ዜጋ ለማፍራት በሚያስችል መልኩ የዘርፈ ብዙ ምላሽ ተግባራትን በየደረጃው ለሚገኘው የማህበረሰብ ክፍል ተደራሽ ለማድረግ በየቀበሌው የማህበረሰብ ውይይት ሳይቆራረጥ ቀጣይነት ባለው መልኩ ማካሄድ ትኩረት የተሰጠው ተግባር ነው፡፡ እንዲሁም የተጠናከረና ተከታታይነት ያለው የማህበረሰብ ውይይት በልማት ቡድኖች በሳምንት 2 ጊዜ ለማካሄድ ታቅዶ 90% ተግባራዊ ማድረግ ተችሎአል፡፡ በበጀት አመቱ በ3,926 ቀበሌያት የማህበረሰብ ውይይትን አጠናክሮ ለማካሄድ ታቅዶ በ3,774 /96%/ ቀበሌያት ላይ ለማካሄድ ተችሎአል፡፡ በማህበረሰብ ውይይት በበጀት አመቱ 1.86 ሚሊዮን የማህበረሰብ ክፍሎችን ለመድረስ ታቅዶ በአስራ ሁለት ወራት 1,272941 /ወንድ 693,020 እና ሴት 579,921/ በማህበረሰብ ውይይት ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ በዚህም የእቅዱን 68% መሸፈን ተችሎአል፡፡ የማህበረሰብ ውይይትን አጠናቅቀው እቅድ አውጥተው የሚንቀሳቀሱ ቀበሌያትን በተመለከተ 3,936 ቀበሌያት እቅድ ያዘጋጃሉ

ተብለው የተያዙ ሲሆን ከእነዚህ መካከል 3,536 /90%/ እቅድ አውጥተው ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ገብተዋል።

በበጀት አመቱ ለ4,830 የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የማህበረሰብ ውይይት አመቻችነት መሰረታዊ ስልጠና እና ለ 3,022 የማነቃቂያ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 100% ተከናውኖአል። በየደረጃው በተፈጠረው የጤና ልማት ቡድንና የ1ለ5 አደረጃጀት በመጠቀም ለማህበረሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችን ለመስጠትና የህዝብ ንቅናቄ በማካሄድ 9.6 ሚሊዮን የክልሉን ማህበረሰብ ተደራሽ ለማድረገ ታቅዶ 10 ሚሊዮን /104%/ ሰዎችን ተደራሽ ማድረግ ተችሎአል።

ከማህበረሰብ ውይይት አንጻር ከታዩ ዋና ዋና ክፍተቶች መካከል የልማት ቡድኖችንና የ1 ለ 5 አደረጃጀቶችን አጠናክሮ ለውይይት አለመጠቀም፣ ውይይት የጀመሩ ቡድኖች እቅድ እስከማውጣት ድረስ ሳይንጠባጠቡ መቀጠል አለመቻል፣ ውይይት ያጠናቀቁትም ቢሆን ባወጡት እቅድ መሰረት አለመንቀሳቀስ፣ የአመቻቾች በተለያዩ ደራሽ ስራዎች መጠመድ፣ የክትትል ማነስ እንዲሁም ሪፖርት በአግባቡና በወቅቱ ለሚመለከተው አካል አለመላክ ሲሆኑ እነዚህን ጉድለቶች ለመቅረፍ የተጠናከረ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ።

በክልል ውስጥ ያሉ መስሪያ ቤቶች ሁሉም በስትራቴጂክና አመታዊ እቅዳቸው ውስጥ የኤች አይ ቪ ኤድስን ጉዳይ በማካተት እየተገበሩ ይገኛሉ። እንዲሁም ሁሉም በክልል ደረጃ የሚገኙ የመንግስት መ/ቤቶች 0.5 በመቶ የመንግስት ሰራተኞች ድጋፍና እንክብካቤ ፈንድ እያዋጡ ሲሆን ሁሉም ከበጀታቸው 2 ከመቶ በመመደብ ኤች አይ ቪ ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ስራ በማጠናከርና በመደገፍ ላይ ይገኛሉ።

የመንግስት ሰራተኞች የድጋፍና እንክብካቤ ፈንድን በተመለከተ በአጠቃላይ ከክልል እስከ ወረዳ ባሉት የአስተዳደር እርከኖች ከሚገኙ የመንግስት ሰራተኞች ፈንዱ ከተቋቋመበት ጀምሮ ከ12 ሚሊየን ብር በላይ ለመሰብሰብ የተቻለ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በክልላችን 674 ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸው የመንግስት ሰራተኞችና ቤተሰቦቻቸው የዚህ ፈንድ ተጠቃሚ በመሆን ላይ ናቸው። እስከ ዛሬ የተዋጣው ገነዘብ አነስተኛ ነው ባይባልም ተመርምረው እራሳቸውን ይፋ የሚያደርጉና የዚህ ፈንድ ተጠቃሚ የሆኑ የመንግስት ሰራተኞች ቁጥር አሁንም እጅግ አነስተኛ በመሆኑ በቀጣይ ሰራተኛው በስፋት እንዲመረመርና ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸው ሰራተኞች የፈንዱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማነሳሳት ስራ ተጠናክሮ የሚሰራ ይሆናል።

በበጀት አመቱ የኤች አይ ቪ ኤድስ የምክርና ምርመራ አገልግሎትን ለ2 ሚሊየን ህዝብ ለማድረስ የታቀደ ሲሆን ለ2,123,373(106.5%) ሰዎች አገልግሎቱን ለማድረስ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ ከተመረመሩት ሰዎች መካከል 1,007,625 (48%) ወንዶች ሲሆኑ 1,115,748 (52%) ሴቶች ናቸዉ:: ከተመረመሩት ሰዎች ዉስጥም 7,510(0.4%) ቫይረሱ በደማቸዉ የተገኘባቸዉ ሲሆን ከእነዚህም ወንዶች 3,235 (43%) እና ሴቶች 4,275(56.6%) ሲሆኑ አስፈላጊዉ በባለሙያ ክትትል እየተደረገላቸዉ ይገኛል::

በበጀት አመቱ በአጠቃላይ በክልሉ በ406 ጤና ተቋማት የኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ ቫይረሱ እንዳይተላለፍ የሚከላከለውን አገልግሎት ተጠናክሮ በመሰጠት ላይ ሲሆን ይህንኑ ለማሳካት የተፋጠነ እቅድ በማዘጋጀት ወደ ስራ በመግባት በክልሉ የሚገኙ ነፍሰጡር እናቶችን በመመርመር ቫይረሱ ለሚገኝባቸው የመከላከያ አገልግሎቱን እንዲያገኙ ለማድረግ ተወጥኗል:: በዚህም በበጀት አመቱ 261,385 ነፍሰጡር እናቶች የምክርና የምርመራ አገልግሎት ያገኙ ሲሆን ከእነዚህም መካከል 1,586 /0.7%/ እናቶች ቫይረሱ በደማቸዉ የተገኘባቸዉ ናቸዉ:: ቫይረሱ በደማቸዉ ከተገኘባቸዉ 1,586 እናቶች መካከል 825 /52%/ የመከላከያ አገልግሎቱን ያገኙ ሲሆን ቀሪዎቹ በክትትል ላይ ይገኛሉ:: በዚህ አገልግሎት ተጠቃሚነት ረገድ የሚታየውን ማነቆ በመፍታት አንድም እናት በወሊድ ምክንያት መሞት እንደሌለባትና አንድም ህጻን ከቫይረሱ ጋር መወለድ እንደሌለበት ታሳቢ በማድረግ የተሰራው ሰፊ ሥራ የንቅናቄ ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ ይህም ካለፉት ጊዜያት በአንጻራዊነት የተሻለ አፈጻጸም ያሳያል፡፡

በበጀት አመቱ ቫይረሱ በደማቸው ለሚገኝባቸውና ለኤድስ ህሙማን የኤች አይ ቪ መራባትን በመቀነስ የሰውነት በሽታን የመከላከል አቅም በማጠናከር ታማሚዎች በተጓዳኝ በሽታዎች እንዳይጠቁ የሚረዳውን የጸረ ኤች አይ ቪ ህክምና አገልግሎት የሚሰጡ የጤና ተቋማትን ቁጥር ከ135 ወደ 171 ለማሳደግ ተችሏል፡፡ በዚሁ መሰረት በእነዚህን ተቋማት በመጠቀም በክልላችን በአሁን ወቅት በአጠቃላይ ለ56,097 አዲስና ነባር ለሆኑ ቫይረሱ በደማቸዉ የሚገኝ ሰዎች የቅድመ ኤች.አይ.ቪ ክብካቤ አገልግሎት በማግኘት ላይ ይገኛሉ:: በአሁኑ ወቅት 23,016 የሚሆኑ ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸው ሰዎች የጸረ ኤች አይ ቪ ኤድስ ህክምና አገልግሎትን እያገኙ ናቸው:: ከአገልግሎት ተጠቃሚነት አንጻር አፈጻጸሙ ከአመት አመት እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም አሁንም አገልግሎቱን እንዲጠቀሙ ከሚጠበቁት ተጠቃሚዎች ቁጥር አንጻር ይህ በጣም ዝቅተኛ አፈጻጸም ስለሆነ በቀጣይነትም መድሎና ማግለልን በማስቀረት እና አገልግሎቱን የበለጠ ተደራሽ በማድረግ ህክምናውን መጠቀም ያለባቸውን ዜጎች ሁሉ ታሳቢ ያደረገ ሥራ ማከናወን ይገባል::

የኤችአይቪ ኤድስ ስርጭት ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ የተለያዩ ዘርፈ ብዙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን እያስከተለ መቆየቱና በማስከተልም ላይ እንዳለ ከማንም የተሰወረ አይደለም:: እነዚህን ችግሮች ለመፍታት በክልላችን በርካታ የድጋፍና እንክብካቤ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ:: ወላጆቻቸውን አጥተው ለችግር የተጋለጡ ሕጻናት በመንግስት& በህብረተሰብና በአጋሮች የተለያዩ ድጋፎችን እንዲያገኙ እየተደረገ የሚገኝ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ለ277,338 ወላጅ አጥ ሕፃናት የትምህርት ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 76,537 (27.6%) የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ እንዲሁም ለ81,088 ያህሉ ወላጅ አጥ ሕፃናት የምግብ ድጋፍ ለማድረግ በእቅድ የተያዘ ሲሆን 38,106 (47%) ተጠቃሚ ሆነዋል::

በተመሳሳይም ሴትኛ አዳሪዎችና ተጋላጭ ሴቶች ከገቡበት አስከፊ ሕይወት ውስጥ መውጣት የሚያስችላቸውን መሰረታዊ ስልጠና በማግኘትና በተለያዩ ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ስራዎች መሰማራት የሚያስችላቸውን ክህሎት ከጥቃቅንና አነስተኛ ብድር ተቋማት ጋር በተቀናጀ ሁኔታ የተሰጣቸው ሲሆን በዘጠን ወራት ውስጥ 817 የሚሆኑ ሴትኛ አዳሪዎች እና 2,126 የደሃ ደሃ የሆኑ ተጋላጭ ሴቶች በድምሩ 2,943 (46%) ሴቶች የገቢ ማስገኛ ስልጠና ተሰጥቷቸው የመንቀሳቀሻ ገንዘብ ድጋፍ ተደርጎላቸው ወደ ስራ ገብተዋል:: በአጠቃላይ በድጋፍና እንክብካቤ ስራዎች ዙሪያ ከሚስተዉሉ ችግሮች መካከል የጠባቂነት ስሜት መኖርና የማህበረሰቡን አቅምና ሃብት አለመጠቀም& የድጋፍና እንክብካቤ ስራዎችን ቀጣይነት ባለው መልኩ አለማካሄድ& የክትትል ማነስና ድጋፍ የሚሰጣቸው ወገኖች ዘላቂነት ባለውና ከተረጂነት ሊያላቅቃቸው በሚያስችላቸው የገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ እንዲያተኩሩ አለማድረግ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ይህንን አመለካከት ለመቅረፍ በቀሪ ወራት የተቀናጀ ስራ መስራት ይጠበቅብናል::

## የቲቢ በሽታን የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባራት

በ2004 በጀት አመት በክልላችን በህብረተሰቡ መካከል ይኖራሉ በሽታውንም በቀላሉ ወደ ሌሎች ጤነኛ ሰዎች ያስተላልፋሉ ተብሎ ከሚገመቱት 18,601 የሳንባ ቲቢ በሽታ ህሙማን መካከል 13,950 የሚደርሱትን በአክታ ምርመራ ለመለየት ከተያዘው እቅድ ውስጥ 9,969 /71.5%/ የሚደርሱትን ለመለየት ተችሏል:: ምንም እንኳን ይህ አፈጻጸም ካለፉት ዓመታት እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም በሽታውን የህብረተሰባችን የጤና ችግር አለመሆኑ እስክናረጋግጥ እና በዘለቄታዊነት የመከላከልና የመቆጣጠር ሁኔታው እስኪጨበጥ ድረስ ሁለት ሳምንትና ከዚያ በላይ ሳል ያለባቸዉን ህሙማን ለምርመራ ወደ ጤና ተቋም መምጣት የሚችሉበትን ሁኔታ

የማጠናከሩና እና በባለሙያም ሆነ በህብረተሰቡ ዘንድ የጠራ ግንዛቤ የመፍጠሩ ተግባር በጤና ልማት ሰራዊት ታጅቦ መፈጸም ያለበት ተግባር ይሆናል።

## የጤናው ሴክተር የፋይናንስ ሪፎርም ተግባራት

ከጤናው ሴክተር የፋይናንስ ሪፎርም ተግባራትን መካከል በማህበረሰብ ዐቀፍ የጤና መድህን ረገድ የተከናወኑትን ተግባራት ስንመለከት የማህበረሰብ ዐቀፍ የጤና መድህን በአነስተኛ ገቢ የሚተዳደሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ለዚሁ አላማ በተቋቋሙ ተቋማት አማካኝነት በአባልነት ተመዝግበው በመደበኛ ሁኔታ በሚያዋጡት መዋጮ መሰረት ከፍተኛ ለሆነ የሕክምና ወጪ ሳይዳረጉ የሕክምና አገልግሎት የሚያገኙበት የአሰራር ስርዓት ነው። ይኸው ሥርዓት የአገልግሎት አቅርቦቱን ከክፍያ ሥርዓቱ በመለየት ህብረተሰቡ ያለ እንግልትና ውጣ ውረድ የጤና አገልግሎቱን እንዲያገኝ ያስችላል። በክልሉ ውስጥ ተቋሙ በሙከራ ደረጃ እንዲመሰረት በተመረጡ 3 ወረዳዎች ማለትም ይርጋለም ከተማ፣ ዳምቦያ ወረዳና ዳሞት ወይዴ ወረዳዎች የሙከራ ትግበራውን ለማሳካት በርካታ ተግባራት በክልል፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ተከናውነዋል። በዚሁ መሰረት ከ3ቱም ወረዳዎች በድምሩ 16,344 ሰዎች በአባልነት ተመዝግበዋል፣ ከተመዘገቡትም አባላት በድምሩ 1,567,352 ብር መዋጮ ተሰብስቧል። በዚሁ መሰረት በ3ቱም ወረዳዎች የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድን ተጠናክሮ ተግባራዊ በመደረጉ በድምሩ 40,912 የጤና መድህኑ አባላት በአቅራቢያቸው ከሚገኙት ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል።

## የመድሃኒት እና የህክምና መሳሪያዎች አቅርቦት

በ2004 ዓ.ም በጀት ዓመት ከተለያዩ የገንዘበ ምንጮች የተገዙ ግምታቸው ብር 411,630,097 የሆኑ መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያ ቁሳቁሶች ወደ ክልሉ ጤና ቢሮ ገቢ የተደረጉ ሲሆን የብር 216,049,668 ግምት ያላቸዉ ደግሞ ለዞን፣ ልዩ ወረዳና ሆስፒታሎች ተከፋፍሏል። ከነዚህም ውስጥ ለኤች አይ ቪ ምርመራ የሚውሉ ሪኤጀንቶች፣ ለወባ በሽታ፣ ለመደበኛ እና ለዘመቻ አገልግሎት የሚውሉ የክትባት መድሃኒቶችና ቁሳቁሶች አብዛኛውን የበጀት መጠን የሚይዙ ሲሆኑ የተቀረዉ ደግሞ ለቤተሰብ ጤና ክብካቤ፣ ለሳንባ በሽታና ስጋ ደዌ ህክምና የሚውሉ መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያ ቁሳቁሶች ናቸዉ። የህክምና መሳሪያዎች አቅርቦትን በተለመለከተ ግንባታቸዉ ከተጠናቀቁት 395 ጤና ጣቢያዎች መካከል 374 (95%) ደረጃዉን በጠበቀ የህክምና መሳሪያዎች እንዲደራጁ ተደርጎ ስራ የጀመሩ ሲሆን የተቀሩትን 61 ጤና ጣቢያዎች እስከ ሀምሌ አጋማሽ ለማሟላት አስፈላጊው ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

## የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ማስፋፋት

በክልሉ የተፋጠነ የመሰረታዊ ጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ለማዳረስ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ሲሆን በበጀት አመቱም የዚህ ተግባር አካል የሆነውን ከዚህ ቀደም ተጀምረው ያልተጠናቀቁ 144 ጤና ጣቢያዎች ለማጠናቀቅና በክልሉ የጤና ጣቢያ ሽፋን 100% ለማድረስ ዕቅድ ተይዞ ወደ ስራ ስሰራ ቆይቷል:: ከእነዚህም ካልተጠናቀቁት ጤና ጣቢያዎች መካከል 82 በቀርቡ በክልሉ መንግስት በጀት የተጀመሩ፤ 31 በክልሉ መንግስት የበጀት ድግፍ ከአመታት በፊት ተጀመሩና ሲንከባለሉ የቆዩ፤ እንዲሁም 31 በፌዴራል መንግስት በጀት ድጋፍ የተጀመሩ እና ሳይጠናቀቁ የቆዩ ናቸዉ::

በበጀት አመቱም በፌዴራል መንግስት የበጀት ድጋፍ ከሚገነቡት መካከል የ14፤ በ2003 ዓ/ም ከተጀመሩት ከ82ቱ ጤና ጣቢያዎች መካከል 21 እና በኤዲቢ ከተጀመሩት መካከል 8 በድምሩ የ43 ጤና ጣቢያዎች ግንባታ የተጠናቀቁ ሲሆን ቀሪዎቹን ጤና ጣቢያዎች በሚጠ ናቀቁበት ሁኔታ ላይ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመቀናጀት ጥረት የተደረገ ይገኛል::

በክልሉ መንግስት በጀት ድጋፍ ሲገነቡ ከነበሩት 146 ጤና ጣቢያዎች መካከል 133 ተጠ ናቅቀው ለአገልግሎት የበቁ ሲሆኑ የተቀሩት 13 ጤና ጣቢያዎች ለበርካታ ጊዜያት የተጓተቱ በመሆናቸዉ እነዚህኑ ጤና ጣቢዎች በበጀት ዓመቱ ማጠናቀቅ ይቻል ዘንድ የሁሉንም የግንባታ ዉለታ በማቋረጥና ቀሪ ስራዎችን ለይቶ በማዉጣት 8ቱ ለአዳዲስ ተቋራጮች ተላልፎ የተሰጡ ሲሆን የ5ቱ ጤና ጣቢያዎች የቀሪ ስራዎች ሰነድ ለዞኖች ተላልፎ የተሰጠ በመሆኑ በዞኖች በኩል ስራዉን ለማስቀጠል በሂደት ላይ ይገኛል:: ሆኖም ከኮንትራት አስተዳደር ጋር በተያያዘ ግንባዎችን ለተራዘመ ጊዜ ካዘገዩ ኮንትራክተሮች ጋር ያለንን ውለ አቋርጠን ለአዳዲሶቹ ተሰጥቶ ሥራ ንዲጀመር የሚደረገዉ ጥረት በኮንትራት ሠነድ ዝግጅት መዘግት ምክንያት በሚፈለገዉ ፍጥነት ሊሄድ አልቻለም::

እስከአሁን በተደረገዉ ጥረት እና ነባር ጤና ጣቢዎችን በመጨመር በክልሉ የመንግስት የጤና ጣቢያዎች ቁጥር 551 የደረሰ ሲሆን የተጠናቀቁትን በግብዓት የማሟላቱ ስራ ጎን ለጎን ተቀናጅቶ እየተፈጸመ የሚገኝ ሲሆን በአጠቃላይ 374 ጤና ጣቢያዎች የተሟላ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች ገብቶላቸዉ ለአገልግሎት ብቁ ንዲሆኑ የተደረገ ይገኛል::

በበጀት አመቱ በወረዳ ማዕከል የሚገኙ 50 ጤና ጣቢያዎችን ወደ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ለማሳደግ ዕቅድ ተይዞ የነበረ በመሆኑ የ50 ዎቹም ጨረታ ወጥቶና አሸናፊዎች ተለይተዉ የግንባታ የውል ስምምነት ተፈራርመው ወደ ግንባታ ገብተዋል ጨረታ ወጥቶ የሰነድ ሽያጭ እየተከናወነ ይገኛል::

በክልሉ ወስጥ በፌደራል እና በክልሉ መንግስት የበጀት ድጋፍ አማካይነት እየተገነቡ ከነበሩት 431 አዳዲስ ጤና ጣቢያዎች ውስጥ እስካሁን የግንባታ ሥራቸው ተጠናቅቆ ርክክብ ከተካሄደላቸው 394 ጤና ጣቢያዎች ለ374 /95.4%/ ጤና ጣቢያዎች በተያዘላቸው ዕቅድ መሠረት ከመድኃኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ /PFSA/ ሀዋሳ ቅርንጫፍ ጋር በመተባበር ደረጃቸውን የጠበቁ የሕክምና መሣሪያዎች ተሰራጭቷል::

## የጤናና ጤና ነክ አገልግሎቶችና ግብዓቶች ጥራት ቁጥጥር ተግባራት

ጤናና ጤና ነክ አ/ግ/ጥ/ቁ/ባለስልጣን በአዲሱ የመሠረታዊ አሠራር ሥርዓት ለዉጥ (BPR) ቅየሳ መሠረት የጤናና ጤና ነክ አገልግሎቶች፣ የጤናና ጤና ነክ ተቋማት፣የጤና ባለሙያዎች፣ የግብአቶች ጥራት ቁጥጥርና አደረጃጀት እንዲሁም አጠቃላይ የጤናና ጤና ነክ አገልግሎት ተደራሽነት ደካማና ጠንካራ ጎኖችን በመፈተሽና በመገምገም የተሻለና ጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት የህብረተሰቡን የጤና አገልግሎት ፍላጎት በማርካት፣ የጤናና ጤና ነክ አገልግሎቶችን፣ የጤናና ጤና ነክ ተቋማትን፣ ጤና ባለሙያዎችን፣ ምግብና መድሃኒትቶችን ጥራ ቸውን፣ ከባለሙያ፣ ከህንጻው፣ ከአገልግሎት አሰጣጥ፣ ከግብአት አንጻር የወጣውን ስ ንዳርድ ማሟላ ቸውን በመቆጣጠርና ደህንነ ቸውን በማረጋገጥ፣ ንዲሁም ከሙያ ስነ ምግባር ውጭ የሚፈፀሙ ተግባራትን በመከላከል፣ የአከባቢ ጤና አጠባበቅ፣ ከተቋማት የሚወጡ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ በስ ንዳርዱ መሰረት መፈጸሙን በመቆጣጠር፣ የማስፈፀሚያ ህጎችን በማጠናከርና የአደገኛ መድሃኒቶች ዝውውርና ህጋዊ ያልሆነ አጠቃቀምን በመከላከል፣ ህብረተሰቡ በተቋሙ ላይ ያለው አመኔ ንዲጨምር ማድረግን ትኩረት ያደረገ ዕቅድ ነው::

በባለስልጣኑ ለበጀት አመቱ የተጣሉ ግቦች በክልላችን ዉስጥ የሚያገለግሉ ነባርና አዲስ ተቀጣሪ የጤና ባለሙያዎች የእውቀትና የክህሎት ደረጃ ወደ 100% ማድረስ፤ ጤናና ጤና ነክ ተቋማት ቅድመ ቁጥጥር በማድረግ የወጣላቸውን ስታንዳርድ ሲያሟሉ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት፤ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የጤናና ጤና ነክ ድርጅቶች በዓመት ውስጥ ቢያንስ አራት ጊዜ በወጣላቸው ስታንደርድ መሰረት ድህረ-አገልግሎት ቁጥጥር ማካሄድ፤ የምግብና መጠጥ ድርጅቶች የጥራት ቁጥጥር ሽፋን 100% ማድረስ፤ አገልግሎት ላይ የዋሉ መድኃኒት፣ ምግብና የምግብ ውጤቶች ቅኝታዊ አሰሳ በዓመት አራት ጊዜ ማካሄድ፤ የተጠረጠሩ ምግቦችና የምግብ ውጤቶች ናሙና ተወስዶ በማስመርመር ውጤቱን ለህብረተሰቡ በአስራ ሰባት ቀናት ውስጥ መግለጽ፤ የባህል መድኃኒት አዋቂዎች ምዝገባ 100% ማድረስ ዋና ዋናዎቹ ነበሩ::

በበጀት ዓመቱ ለጤና ባለሙያዎች የሙያ ምዝገባና ፈቃድ ምስክር ወረቀት መስጠትና ማደስ ለአዲስ ጤና ባለሙያዎች የሙያ ምዝገባና ፈቃድ ምስክር ወረቀት መስጠትን በሚመለከት ለ5250 የድፕሎማ ጤና ባለሙያዎች ለመስጠት ታቅዶ ለ994 ባለሙያዎች የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙ 18.9% ደርሷል፡፡ ለ1340 ድግሪ ተመራቂ ጤና ባለሙያዎች የሙያ ምዝገባና ፈቃድ ምስክር ወረቀት ለመስጠት ታቅዶ ለ210 ለተለያዩ የጤና ባለሙያዎች ለመስጠት ተችሏል፡፡ በተጨማሪ የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ክልሎች ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የፓናል ዉሳኔ እንዲሰጡ በወሰነዉ መሠረት ከተለያዩ የመንግስትና የግል ትምህርት ተቋማት በመደበኛና በተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም ተከታትለዉ በመጀመሪያና በሁለተኛ ድግሪ የሙያ ማሻሻያ ላደረጉ የፓናል ኮምቴ የቀረቡትን መረጃዎችና የአገልግሎት ዘመናቸዉን ካጣራ በኋላ በበጀት ዓመቱ ለ167 የመጀመሪያ ድግሪ፣ ለ14 ሁለተኛ ድግሪና ለ24 ድፕሎማ ባለሙያዎች ተሰጥቷል፡፡ የድፕሎማ ጤና ባለሙያ ተመራቂዎችን በተመለከተ የአፈፃፀም ዝቅተኛነት የታየዉ ዕቅዱ የተያዘዉ በክልላችን ዉስጥ ካሉ ከመንግስትና ከግል ጤና ተቋማት የሚመረቁ ባለሙያዎችን ቁጥር ታሳቢ አድርጎ የነበረ ቢሆንም ማስረጃዉ የሚሰጠዉ የልህቀት ምዘና ፈተና ወስደዉ ላለፉ ብቻ በመሆኑ ዝቅተኛ አፈፃፀም ሊመዘገብ ችሏል፡፡

በመንግስትና በግል ጤና ተቋማት በማገልገል ላይ የሚገኙ ነባር የጤና ባለሙያዎች የሙያ ምዝገባና ፈቃድ ምስክር ወረቀት በየአምስት ዓመት የሚታደስ ስለሆነ ባለሙያዎች ወቅቱን ጠብቀዉ እንዲያሳድሱ ባለስልጣኑ ክትትል ያደርጋል፡፡ በመሆኑም በዓመት የ765 ባለሙያዎች የሙያ ምዝገባና ፈቃድ ምስክር ወረቀት ለማደስ ታቅዶ ለ239 የጤና ባለሙያዎች እድሳት የተደረገ ሲሆን አፈፃፀሙ 31.2% ይደርሳል፡፡

ለመንግስትና ግል ጤና ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት ጥራት የጠበቀና ቀልጣፋ የጤና አገልግሎት ለህብረተሰቡ ለማስፈን ሁሉም የመንግሰትና የግል ጤና ተቋማት የወጣላቸዉን ስታንዳርድ አሟልተዉ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አዉጥተዉ ማገልገል እንዳለባቸዉ ታምኖበታል፡፡ በመሆኑም በክልላችን ዉስጥ ለሚገኙ ሁሉም የመንግስት ጤና ተቋማት ለ18 ሆስፒታሎች፣ ለ501 ጤና ጠቢያዎችና ለ1165 ጤና ኬላዎች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት ታቅዶ ለ4 ሆስፒታሎች፣ ለ101 ጤና ጣቢያዎችና ለ687 ጤና ኬላዎች ተሰጥቶአል፡፡

ለግል ጤና ተቋማትንም በተመለከተ ለ134 መለስተኛ ክሊኒክ፣ ለ55 መካከለኛ ክሊኒክ፣ ለ10 ከፍተኛ ክሊኒክ፣ ለ24 ገጠር መድኃኒት ቤት፣ ለ86 መድኃኒት መደብር፣ ለ8 ፋርማሲና ለ41

መለስተኛ ዲ/ላቦራቶሪ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት ታቅዶ ለ125 መለስተኛ ክሊኒክ፣ ለ40 መካከለኛ ክሊኒክ፣ ለ3 ከፍተኛ ክሊኒክ፣ ለ11 ገጠር መድኃኒት ቤት፣ ለ37 መድኃኒት መደብር፣ ለ2 ፋርማሲና ለ11 መለስተኛ ዲ/ላቦራቶሪ ተሰጥቶአል፡፡

ከዚህ ቀደም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አግኝተዉ በማገልገል ላይ የሚገኙ የመንግስት ጤና ተቋማት ዉስጥ ለ191 ጤና ጣቢያና ለ1204 ጤና ኬላ ለመስጠት ታቅዶ ለ119 ጤና ጣቢያና ለ543 ጤና ኬላ እድሳት ተደርጎላቸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ለ813 መለስተኛ ክሊኒክ፣ ለ133 መካከለኛ ክሊኒክ፣ 18 ከፍተኛ ክሊኒክ፣ ለ154 ገጠር መድኃኒት ቤት፣ ለ189 መድኃኒት መደብር፣ ለ22 ፋርማሲ፣ለ3 መካከለኛ ዲ/ላቦራቶሪና ለ70 መለስተኛ ዲ/ላቦራቶሪ እድሳት ለማድረግ ታቅዶ ለ789 መለስተኛ ክሊኒክ፣ ለ124 መካከለኛ ክሊኒክ፣ 18ከፍተኛ ክሊኒክ፣ ለ154 ገጠር መድኃኒት ቤት፣ ለ187 መድኃኒት መደብር፣ ለ20 ፋርማሲ፣ለ3 መካከለኛ ዲ/ላቦራቶሪና ለ68 መለስተኛ ዲ/ላቦራቶሪ እድሳት ተደርጎላቸዋል፡፡

ሁሉንም የጤና ተቋማት በበጀት ዓመት ቢያንስ አራት ጊዜ ቁጥጥር ለማድረግ የታቀደ በመሆኑ ለ15 ሆስፒታሎ፣ ለ587 ጤና ጣቢያዎች፣ ለ3279 ጤና ኬላዎች የጥራት ቁጥጥር ስራ ተካሂዷል፡፡ በግል ጤና ተቋማትም ለሆስፒታል 32ጊዜ፣ ለመለስተኛ ክሊኒክ 2068ጊዜ፣ ለመካከለኛ ክሊኒክ 387ጊዜ፣ ለከፍተኛ ክሊኒክ 65ጊዜ፣ ለገጠር መድኃኒት ቤት 511ጊዜ፣ ለመድኃኒት መደብር 589ጊዜ፣ ለፋርማሲ 120ጊዜ፣ ለመካከለኛ ዲ/ላቦራቶሪ 11ጊዜና ለመለስተኛ ዲ/ላቦራቶሪ 215ጊዜ ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ 8 ጊዜ በሆስፒታል፣ 1867 ጊዜ በመለስተኛ ክሊኒክ፣ 336 ጊዜ በመካከለኛ ክሊኒክ፣ 57 ጊዜ በከፍተኛ ክሊኒክ፣ 475 ጊዜ በገጠር መድኃኒት ቤት፣ 546 ጊዜ በመድኃኒት መደብር፣ 24 ጊዜ በፋርማሲ፣ 11 ጊዜ በመካከለኛ ዲ/ላቦራቶሪና 181 ጊዜ በመለስተኛ ዲ/ላቦራቶሪ የጥራት ቁጥጥር ተካሂዷል፡፡

በክልላችን በሁሉም ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች የሚገኙ የጤና ነክ ተቋማት እጅግ በርካታና ከነባራዊ ሁኔታ በመነጨ ስታንዳርዱን የጠበቁ ባለመሆናቸዉ ለቁጥጥር ሥራ አስቸጋሪ ቢሆኑም እንኳን እንደጤና ተቋማት ሁሉ በበጀት ዓመት አራት ጊዜ ለ21745 (21745*4=86980) የግል ጤና ነክ ተቋማት ላይ ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ 56357 ጊዜ የጥራት ቁጥጥር ተደርጓል፡፡ ለእነዚህ ሁሉ የጤና ነክ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የታቀደ ሲሆን በደንቦችና በመመሪያዎች ግልፀኝነት መጓደል የተነሳ ከንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ጋር የባለቤትነት ድርሻ ተለይቶ ባለመቀመጡ ሊሳካ አልቻለም፡፡

በበጀት አመቱ ተደረገው የቁጥጥር ስራ በህገ ወጥ መንገድ ሲዘዋወር የተገኘ የተለያየ አይነት በርካታ ቁጥር ያለዉ መድኃኒትና አልሚ ምግብ በዲላ፣ በይርጋዓለም፣ በአለታ ወንዶ፣ ወላይታ ሶዶና አርባ ምንጭ ከተማዎች የተገኘ ሲሆን ጉዳዩ በህግ እየተጣራ ይገኛል፡፡ እንዲሁም በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር 3 የባህል ህክምና አዋቂዎች ነን ባዮች ምንነቱ በዉል የማይታወቅ ባህላዊ መድኃኒት ይዘዉ ከመገኘታቸዉ በላይ ዘመናዊ የህክምና አገልግሎት በመስጠትና በርካታ ያልተፈቀዱ ተግባራትን ሲፈፅሙ በመገኘታቸዉ ከሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ጽ/ቤትና ከፖሊስ ጋር በመተባበር ችግሩን ከምንጩ ለማድረቅ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይህም የባህላዊ ህክምና አገልግሎት ከፍተኛ የአሠራር ችግር ያለበትና በክልላችን በአብዛኛዎቹ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ተስፋፍቶ የሚገኝ በመሆኑ በዘርፉ ሊኖር ስለሚገባዉ የአሰራር፣ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓትን በተመለከተ የአሰራር መመሪያ ለዞኖችና ልዩ ወረዳዎች የተላለፈላቸዉ ሲሆን አፈፃፀሙም ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

## የህብረተሰብ የላቦራቶሪ ምርመራ ተግባራት

ጤና ላቦራቶሪ የስራ ሂደት ዋነኛ ግቡ ውጫዊ የላቦራቶሪ ጥራት ቁጥጥር አገልግሎት በሁሉም የጤና ተቀማት እንዲኖር ማስቻል የሚከሰቱ ወረርሽኞች ታማኝነት ያለው የላቦራቶሪ ውጤት በወቅቱ ማቅረብና የላቦራቶሪ ምርመራ ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ ለማካሄድ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ማካሄድ ነው:: የሕብረተሰብ ጤና ላቦራቶሪ ከሚያከናውናቸው ዋናዋና ተግባራት መሀከል ትኩረት ሰጥቶ ከሚንቀሳቀስባቸው የጤና ልማት ዘርፎች የሚከተሉት ይገኛሉ::

የቲቢ ምርመራ ውጫዊ ጥራት ቁጥጥር *(EQA)* ስራን በተመለከተ የክልሉ የሕብረተሰብ ጤና ላቦራቶሪ በ11 ወራት ውስጥ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ 301 ጤና ተቋማት ላይ የቲቢ ምርመራ ጥራት ቁጥጥር ያከናወነ ሲሆን በጥራት ቁጥጥሩ ወቅት ከተሰበሰቡት 6940 ስላይዶች ውስጥ 6750 /97%/ ስላይዶች ከክልሉ ላቦራቶሪ ውጤት ጋር የተስማሙ ሲሆን 190 ስላይዶች ልዩነት አሳይተዋል:: እንዲሁም በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ የግል ጤና ተቀማት በ27 ጤና ተቋማት ላይ የቲቢ ምርመራ ጥራት ቁጥጥር ያከናወነ ሲሆን በጥራት ቁጥጥሩ ወቅት ከተሰበሰቡት 295 ስላይዶች ውስጥ 293 /99%/ ስላይዶች ከክልሉ ላቦራቶሪ ውጤት ጋር የተስማሙ ሲሆን 2 ስላይዶች ብቻ ልዩነት አሳይተዋል::

የHIV Rapid Test ምርመራ ጥራት ቁጥጥር ስራን በሚመለከት በ11ወራት ውስጥ ለጥራት ቁጥጥሩ የሚረዱ 138 የሴረም (Serum) ናሙናዎችን በማዘጋጀት በክልሉ ለሚገኙ 27 የግል ጤና ተቋማት በማሰራጨት እንዲመርመር የተደረገ ሲሆን የ133 ናሙናዎች ከሕ/ጤ/ላቦራቶሪ ጋር ተመሳሳይ ዉጤት ስኖራቸዉ የ5 ናሙና ብቻ ተቃራኒ በመሆኑ ለባለሙያዉ የስራ ላይ ሥልጠና ተሰጥቶታል፡፡

የወባ በሽታ ምርመራ ጥራት ቁጥጥር ስራ በ88 ጤና ተቋማት ላይ በ44 ፖዜቲቭና 54 ኔጋቲቭ በአጠቃላይ 98 እስላይዶች ላይ የጥራት ቁጥጥር የተካሄደ ሲሆን 92 እስላይዶች ተመሳሳይ ውጤት ሲኖራቸው 06 ደግሞ የውጤት ልዩነት ታይቶባቸዋል፡፡

የጨቅላ ሕፃናት ከ18 ወር በታች የኤች አይ ቪ ምርመራን በ11ወር ውስጥ ለ786 ህጻናት የተሰራላቸዉ ሲሆን 8 ህጻናት ኤች አይ ቪ የተገኘባቸው ናቸው። ከዚሁ በተጨማሪ ለ312 ሰዎች የCD4፣ ለ312 ሰዎች Heamatology እና ለ131 ሰዎች የblood Chemistry ተሰርቶላቸዋል። በበጀት ዓመቱ የባክትሮሎጂ ምርመራ 403 ናሙናዎች ተሰብስቦ ምርመራ የተደረገል፡፡

## የካፒታል በጀት አጠቃቀም

በበጀት አመቱ ለነባርና አዲስ የግንባታ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የተመደበው ጠቅላላ በጀት ብር 316,009,705 ሲሆን ከዚህም ውስጥ ስራ ላይ የዋለው ብር 280,835,603 /89%/ ነዉ። የጤና ጣቢያ ግንባታዎች በሚፈለገዉ ፍጥነት ባለመሄዳቸዉ ምክንያት የክፊያ ጥያቄ በወቅቱ ባለመቅረቡ በተለይ ለነባር ግንባታዎች ማጠናቀቂያ የተያዘውን በጀት በታቀደው መሰረት መጠቀም አልተቻለም።

በበጀት አመቱ የጤና ጣቢያ ጤና ኬላ ትስስር ለማጠናከርና የአገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል 500 ሞተር ሣይክሎች፣ 77 አምቡላንሶች ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለዞኖችና ለልዩ ወረዳዎች ስርጭት ተደርጓል። በተለይም አምቡላንሶቹ የእናቶችና የህጻናትን ሞት በመቀነስ ረገድ የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ለመጡበት አላማ ብቻ እየዋሉ ስለመሆኑ የተከበረው የምክር ቤት አባላት በየአካባቢያቸው ክትትል ሊያደርጉ ይገባል ።

## የሰው ሃብት ልማት

የሰዉ ሃይል ልማት ለአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል ወሳኝ በመሆኑ በበጀት አመቱ የሙያ ማሻሻያ ለማድረግ 640 ባለሙያዎች የክህሎት ክፍተት ማሟያ ስልጠና ለመውሰድ፣ 18

ተማሪዎች በተለያየ የሙያ መስክ ለሙያ ማሻሻያ፣ 12 ባለሙያዎች ከዲፕሎማ ወደ ዲግሪ፣ 18 ባለሙያዎች በተለያየ መስክ ከመጀመሪያ ድግሪ ወደ ሁለተኛ ድግሪ ሙያ ለማሻሻል ገብተዋል:: በሀገሪቱ በጤናው ዘርፍ ያለውን የከፍተኛ ደረጃ ባለሙያዎች እጥረትን ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ የህክምና ሙያ ስልጠና በይርጋዓለም ሀ/ኮሌጅ የተጀመረ በመሆኑ በበጀት አመቱ 60 ተማሪዎች ተቀብሎ የማስተማር ሥራ ጀምሯል:: የሙያ ማሻሻያ አደረገው የተመለሱትን በተመለከተ በበጀት አመቱ 52 ባለሙዎች ከሰርተፍኬት ወደ ዲፕሎማ፣ 178 ባለሙዎች ከዲፕሎማ ወደ ድግሪ፣ 18 ባለሙዎች ከድግሪ ወደ ሁለተኛ ድግሪ ማሻሻያ ትምህርት አጠናቅቀዉ የተመደቡ ሲሆኑ 2185 በደረጃ አራት የብቃት ፈተና ወስደው ያለፉ፣ 38 በድግሪ ደረጃ የተመረቁ ባለሙያዎች፣ 36 ሀኪሞች አዲስ የተመደቡ ናቸዉ::

## የጤና አመራር መረጃ ስርዓት

በበጀት ዓመቱ አዲሱን የጤና አመራር መረጃ ስርኣት በሁሉም አከባቢዎች ለማዳረስ እና መረጃን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ የመስጠት ልምድን ለማጎልበት ታቅዶ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን እስከ በጀት አመቱ ማብቂያ የቤንች ማጂ& ከፋ እና ሸካ ዞኖች ሲቀሩ ሌሎችን አከባቢዎች ሙሉ በሙሉ መተግበር የተጀመረ በመሆኑ በክልሉ ሙሉ ትግበራ የጀመሩ ጤና ተቋማትን ሽፋን በጤና ጣቢያዎች 85%፣ በሆስፒታሎች 83% እና በጤና ኬላዎች የማህበረሰብ ጤና መረጃ ሥርዓትን መተግበር የጀመሩ ጤና ኬላዎች ብዛት 2500 /69%/ ደርሷል:: በቀሪዎቹም አከባቢዎች ይህንን ተግባር ለማዳረስ የህትመት ዉጤቶች ተጠናቀቀዉ የገቡ በመሆኑ የማነቃቂያ ስልጠና በመስጠት ትግበራ ለመጀመር ጥረት እየተደረገ ይገኛል::

## የጥናትና ምርምርን ተግባራት

በበጀት ዓመቱ በጤናዉ ሴክተር የተለዩ 5 ችግር ፈቺ ጥናቶችን ማከናወን የተጠኑ ግን ህትመት ያልተካሄደላቸው 3 ጥናቶችን ማሳተምና ማሰራጨት በጤና ነክ ጉዳዮች ላይ ምርምር ለማድረግ የሚቀርቡ የጥናት ፕሮፖዛሎችን የስነ ምግባር ግምገማ ማከናወን የታቀዱ ዋናዋና ጉዳዮች ሲሆኑ በበጀት ዓመቱ በመፀዳጃ ቤቶች አጠቃቀም ላይ እና በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አተገባበር ላይ የተካሄዱ ክልል አቀፍ ጥናቶችን የማስረጽ ስራ ተሰርቷል:: ከእናት ወደ ልጅ ኤች አይ ቪ እንዳይተላለፍ የመከላከያ አገልግሎት አጠቃቀም ላይ ለሚካሄደው ጥናት መረጃው ተሰብስቦ የትንተና ስራ በመሰራት ላይ ይገኛል:: በጤና ተቋማት የሚሰጠውን የወሊድ አገልግሎት አጠቃቀምን በሚወስኑ ጉዳዮች ላይ ጥናት ለማካሄድ ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎ መረጃ ወደ መሰብሰብ ለመግባት በዝግጅት ላይ ይገኛል::

በሌሎች ለጥናት በተመረጡ ርዕሶች ላይ ጥናት ለማከናወን ፕሮፖዛል የማዘጋጀት ና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመገናኘት የጋራ የሥራ እቅድ በማውጣት የበጀት ማፈላለግና የፓርትነርሽፕ ሥራ እየተሰራ የሚገን ሲሆን የተለያዩ የጥናት ፕሮፖዛል ይዘው የሳይንስና ሥነ ምግባር መረጃ ጥያቄ ለሚያመጡ ግለሰቦችና ድርጅቶች በሳይንስና ስነምግባር ኮሚቴ አማካኝነት መመዘኛውን አሟልተው ለቀረቡት ጥናት እንዲያካሄዱ ፍቃድ ተሰቷቸዋል፡፡

## ያጋጠሙ ችግሮች

በአጠቃላይ ባለፈው የበጀት ዓመት በሴክተሩ የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታ በሚፈለገው መጠንና የጥራት ደረጃ አለመፈጸም ፤የለውጥ መሳሪያዎችን በሙሉ በእዉቀትና ክህሎት አዉቆ አለመምራት፣ በግንባታ ጥራት ቁጥጥርና በኮንትራት አስተዳደር ረገድ የሚታዩ በርካታ ጉድለቶች ከዚህ ጋር በተያያዘም ግንባታዎችን በሚፈለገው ፍጥነትና ጥራት አጠናቅቆ ለአገልግሎት ብቁ አለማድረግ፣ አመራሩና ባለሙያው ፀረ-ኪራይ ሰብሳቢነትን ትግል በሚጠበቀው ደረጃ አለመታገል፤ ከአምቡላንስ አጠቃቀም ጋር ተያይዘው የሚታዩ ችግሮች፣ አዲሱን የጤና መረጃ ስርዓት ወደ ሁሉም አከባቢዎች ማዳረስ አለመቻልና ይህም ለአፈጻጸም ክትትልና ለርፖርት አዘገጃጀት አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደር በበጀት አመቱ በሴክተሩ ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች ናቸዉ፡፡